BADR ETHIOPIA

International Ethiopian Muslims Organization

የ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ድርጅት

(በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነዉ)

## ለወገን ደራሽ ወገን ነዉ

በሀገራችን በተከሰተዉ ድርቅ ምክንያት በርካታ ዜጎች በረሀብ ችግር ዉስጥ መዉደቃቸዉ ከተለያዩ አካላት በይፋ መገለጹ የሚታወቅ ነዉ ። በተፈጠረዉ የዝናብ እጥረት ሳቢያ በርካታ እንስሳት እየሞቱና በህብረተሰቡም ላይ ለሞትና ለተለያዩ ከፍተኛ ጉዳቶች መዳረሱን በተለይ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል እና በአፋር አካባቢዎች መሆኑን ዘጋቢዎች ጭምር ይገልጹታል።

በተፈጥሮ ችግርነት የሚታወቀዉ ድርቅ በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት በማንገዋበብ ትዉልድን ከማፈናቀሉ አልፎ በርካታ ህይወትን በማጥፋት ይታወቃል። አሁን ባለዉ ሁኔታ ችግሩን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ለተራበዉ ማህበረሰብ አቅም በፈቀደ መጠን የምግብ አቅርቦት ሊደረግለት እንደሚገባ ሁሉም ዜጋ በጽኑ ያምናል።

በድር አለም አቀፍ የሙስሊሞች ድርጅትም በሀገራችን የተፈጠረዉን የረሀብ ችግር አሳሳቢነቱን በማጤንና ፈጣን ምላሽ ሊሰጠዉ እንደሚገባም በመገንዘብ “ ለወገን ደራሽ ወገን ነዉ” በሚል መርህ ቃል በዉጭ የሚኖረዉን ማህበረሰብ በማስተባበር ረሀቡን ለመታደግ እንዲቻል እያንዳንዱ የኮምዩኒቲ አካላት በየራሳቸዉ ደረጃ ረሀብ ለተከሰተባቸዉ አካባቢዎች የምግብ አቅርቦት ለመፈጸም ያመቻል ብለዉ በሚያምኑበት መንገድ ሁሉ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ታደርጉ ዘንድ መልእክታችንን እናስተላልፋለን።

በድር አለም አቀፍ የሙስሊሞች ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሰሜን አሜሪካ

NOVEMBER **2015**